# በነሃሴ 16 በጋሻ ለኢትዮጵያውያን ስለተጠራው

# የህዝብ ስብሰባ አጭር ዘገባ

ስብሰባው በጋሻ የህዝብ ግንኙነት ጉዳይ ሓላፊ ኣቶ ዮሃንስ ሓጎስ ከተከፈተ በሃላ የማህበሩ ሊቀመንበር ኣቶ ሱልጣን ኣለነ ጋሻ እስከ ኣሁን ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራትን ኣጠር ኣድርጎው ኣቅርቧል።

በመቀጠልም ፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማርያም ወደ መድረክ በታላቅ ጭብጨባ ኣድማጩ የተቀበላቸው ሲሆን ፕሮፌሰሩም በኢትዮጵያ በመደረግ ላይ ያለውን የሰብኣዊ መብት ጥሰትን አስመልክተዉ ሰፋ ባለ መንገድ ያቀረቡ ሲሆን በተለይም የኣንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር በሆኑት ወ/ሪት ብርቱኳን ሚደቅሳ ጉዳይ በጥልቀት ትንተና ሰጥተውበታል።

የብርቱኳን ሚደቅሳ ለሁለተኛ ጊዜ እንዴት ወደ እስር ቤት አንደገቡ ለተሰብሳቢው ካብራሩ በሃላ፤ በኣጠቃላይ የኢትዮጵያ የህሊና እስረኞች መርዳት የሚቻልበትን ዘዴዎች በዝርዝር ኣቅርቧል። ለጊዜውም ተቆርቁሪ ኢትዮጵያውያን በሁለት ጉዳዮች ላይ ኣተኩረን እንድንቀሳቀስ ነው በጥብቅ



ፕሮፌሰር አለማየሁ በኢትዮጵያ በመደረግ ለይ ባለዉ የሰብኣዊ መብት ረገጣን አስመልከተዉ ሰፊ ንግግር ሲያደርጉ. (ፎቶ፡ጋሻ)

ያስገነዘቡን። በአምባ ገነኑ መንግስት በፖለቲካ ምክንያት የታሰሩት ንጹሃን ኢትዮጵያዉያን ቁጥራቸውም ሆነ የታሰሩበትን ቦታ በማስረጃ የተደገፈ ጥናት በማካሄድ በእስርቤት ቤት ውስጥ እያሉ ከሚደርስባቸው ሰቆቃ ግርፋትና መጠን የለሽ ግፍ ለማላቀቅ እንዴት እንደሚቻል ህጋዊ መንግዶችን ጠቁመዋል።

ሀ. እንደዛሬው በጋሻ እንደተዘጋጀው የህዝብ ስብሰባ፣ እንደዚሁም በቡድንም ሆነ ኣንድ ላኣንድ በሚደረገው የኢትዮጵያውያን ማህበራዊ ግኑኝነት የእስረኞች ኣያያዝ ጉዳይ ሁሌም እንዲነጋገሩበትና ብሎም በምን መልክ ተጽእኖ ማድረግ እንደሚቻል የተለያዩ መንገዶችን መቀየስንና ማፍለቅን፣ ለተግባራዊነታቸውም ሳይታክቱ መንቀሳቀስን.

ለ. ከዚህ በፊት የህሊና ሰለባ በመሆን በእስር ለረጅም ጊዜ የተሰቃዩትን ተዋቂ ሰዎች እንደ ፕረዚደንት ኔልሰን ማንዴላና ዴዝማን ቱቱ እንደዚሁም ስለሰብኣዊ ተፎጥራዊ ነጻነት ግንዛቤኣቸው በጣም ላቅ ያሉትን እንደእነ ፕርዚደንት ኦባማና የመሳሰሉትን በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ እጃቸው እንዲያስገቡ በተደጋጋሚ መወትወትንና ያለማቋዋረጥ ጥሪ ማስተላለፍን የሚሉ ነበሩ። ለወደፊቱ ብዙ ሊከናወኑ የሚገባቸው ተጨማሪ ተግባራት የሚሰነዝሩ መሆናቸውን ኣሳስበው ለጊዜው ግን በነዚህ በተጠቆሙት ሁለት ነጥቦች ላይ ትኩረት እንዲሰጥ በሚል ንግግራቸውን ደምድሟል።

(ስለ ጉዳዩ ይበልጥ እንዲረዱ ይህን ይጫኑ - http://www.ethiopiangasha.org/tmp/ProAL16Aug2009.html)

ሁለተኛው ተናጋሪ ክሪስ ፍላሃሪቲ ሲሆኑ ያተኮርቱም በሰሩት ፊልም ማብራሪያ በመስጠቱ ላይ ነበር። ፊልሙ ብዙ ጉዳዮችን ያጠቃለለ ቢሆኑም ኣቅራቢው ያተኮሩት የምርጫ ፱፯ በሚገልጸው የፊልሙ ክፍል ላይ ነበር። በፊልሙ ቀረጻ ሂደት የገጠሙዋቸው ሁኔታዎች ቀላል እንዳልነበሩም ጨምረው


አቶ ክሪስ ፍላሃሪቲ ለተሰብሳቢዉ ያቀረቡትን "Migration of Beauty" የተሰኘዉን ፊልም ማብራሪያ ሲሰጡ፡ (ፎቶ ፡ ጋሻ)

የገለጹ ሲሆን በተለይም ለቃለ-መጠይቅ የሚፈልግዋቸው ሰዎች ትብብራቸው ኣስቸጋሪ ለመኖሩ ሳይሸሽጉ ተናግሯል። ዋናው ምክንያትም በስልጣን ካለው መንግስት ሊደርስባቸው ስለሚችል ቅጣት ግንዛቤ በማስገባት ለመኖሩ ድብቅ ኣልነበረም በሚል ገለጻቸውን ኣጠቃልለዋል። በውይይት ክፍለ-ጊዜ ብዙ ሰዎች በንቃት የተሳተፉ ሲሆን፡ በኣጠቃላይ የፕሮግራሙ ሁኔታ የተገኙት እንግዶች መርካታቸው በተለያዩ መንገዶች ለኣዘጋጅው ድርጅት ጋሻ ኣስታውቁኣል።

*ኢትዮጵያ በሀቀኛ ልጆቿ ጥረት በአንድነት ፀንታ ትኖራለች !!!*

*ጋሻ ለኢትዮጵያውያን*

*በነሃሴ 16*

http://www.ethiopiangasha.org